# የሃያ ዓመት ውሸት

## *መለስ አባት የለው፤*

መለስ በእርግማን ቢሆን በጸሎት
ቀድሞውን ባልገባ ከቤተ መንግሥት::
የብረት ምሰሶ አይነቅዝም ያሉት
ማን ይነካው ነበር ደርግን በጉልበት::
በሰው ፍቅር ቢሆን በእምነት በአምልኮት
ራስታ ጀማይካ ሃይሌን ባቆዩት::
እንኳንም ተጠልቶ ህዝብን አስመርሮ
እምዬ ምኒልክ ዮሃንስም ኖሮ
አልቀረም ማለፉ በቀነ ቀጠሮ::
ሁሉም ገደብ አለው የጫወታ መግቻ
መለስ አባት የለው ነጋሪ ለብቻ
ተውጦ ሊተፋ በህዝባዊ ዘመቻ
አፍጦ ይጠብቃል ተጎልቶ እንደ ጉልቻ::

## *እርግማን ብዙ:*

የጦሩ አለቃ የደርጎች የበላይ
መንጌ ፈሪ ኖሯል፤ የአምባ ገንን ጸባይ
ሾልኮ አመለጠ ቀዶ በጣራ ለይ::
ያ ሁሉ ድንፋታ ምድር የምጠበው
አምላክ የለም ብሎ አዋጅ ያስነገረው
የዛሬ ህይወቱን ለተመለከተው
ለአምባ ገነን ሁሉ ንስሃ መግቢያ ነው::
ሲመለክ የኖረው እንደ አምላከ ጸሓይ
በቁሙ ሲቀብረው ሥልጣን አታላይ

ተከታዩ ሳይቀር ተነድቶ በተራ
ለአብዮቱ በአል ሲታረድ በቁራ
የቤተ መንግሥቱ ቀጣዩ ተረኛ
እርግማን ብዙ እንዴት ብሎ ተኛ::

## *ለሌሎች ባስማሰው:*

ወንበሩ የመቃ የሌለው ጉልበት
አልጋው አረግራጊ የሌለው መሰረት
ሠራዊቱ ባዶ የአንድ ዘር ውቅር
አናቱ ሲመታ የሚጠፋ ከሥር::
አልለመድ ብሎ ካለፈው መማር
አፈጥጦ መጠበቅ እዚያው ሊቀበር::
እንዴት አይባንንም አይነቃም ወይ ሰው
የራሱን መቃብር አርቆ እየማሰው
መለስ አልተማረ አልገባው ሚስጢር
አምባ ገነን መሪ መቅረቱን በአጭር
ለሌሎች ባስማሰው ገብቶ ሲቀበር::

## *ተራ ሰው ቢሆን:*

ቃል ኪዳን ጠባቂ የአራት ኪሎ ጠጅ
አክብረው ከተዉት አይጎዳም ወዳጅ
አለዚያ ሰይጣን ነው አስብቶ ገዳይ
ሰውየው ምነካው አላወቀም ወይ::
የልጅ ነገር ሆኖ አብዝቶ ጠጥቶ
መራመድ ተስኖት ሊቀርነው ተደፍቶ
ዘሎ የሚቀማ ሃሞተ ቆራጥ

ዛሬ ባይወለድ እናት ባታምጥ
ሲቆዩበት አይወድ የአራት ኪሎ ቤት
ወንድምን ቀይሮ ያደርጋል ጠላት
ቶሎም ካልባነኑ ቀብሩም ሽንት ቤት።
ደፍራችሁ ንገሩት ያቁም መጠጡን
ንስሃ ቢገባ ቀጣዩን ዘመን
ቢቀር ወርቅነቱ ተራ ሰው ቢሆን።

## *ጉድ አለ ከኋላ፡*

ሆነና የልጅ ነገር ብስልና ጥሬ
ክብርና ሞገሱን ሲመኝ ጋሻ ጃገሬ
ጡረታ ሊከበር ሊኖር ተኮፍሶ
እልል ብሎ ሊሸኝ ድግስ ተደግሶ
ህዝብ ተንገሽግሾ መሮት እንደ ኮሶ
የማይታሰብ ነው በደም ለታጠበ
እንኳን አካል ቆርጦ ለባእድ የረጠበ
ለአገር ለተሰዋ ውለታ አልታሰበ።
እንደ ባለውለታ እንዳ ምኑጨዋ
ያለፈው ተረስቶ፤ሊበላ በሁለት ቢላዋ
ጡረታ ሰወጣ ይሰጠኝ መኪና
ሥልጣኔ ይከበር ይሽፈን የቤቴ ገበና
መወትቱ በዛ ጉድ አለ ከኋላ
አዋጅ የማሸረው የፈጣሪ ዱላ።
ከዙፋን አውርዶ መሬት የሚያስተኛ
ጆሮ ያለው ይስማ ተናገረናል እኛ።

## *ሲባል እንዳል ነበር፡*

የጊዜው መቃረቢያ የህልም ላይ ሩጫ
ማምለጫ ሲጠፋው መያዣ መጨበጫ
ኣዲስ ታሪክ ፅፎ ወስኖ በመቶ
እንዳለፈለፈ አንደበቱን ሞለቶ
ምእተ ዓመቱ ይከበር በድምቀት
በዓለም ልዩ ሆነን እንታይ በኩራት
ባንዲራን ጨርቅ አርጎ ቋጥሮባት በርበሬ
ከፍ አርጋችሁ ስቀሉ መኩሪያናት ለአገሬ
ለሰሚው ግራ ነው አይመች ለውሬ::
በጎሳ ከፋፍሎ ሸንሽኖ ጨርሶ
እንደ ምች መደሃኒት እንዳለሰጠ በጥሶ
ለአንድነቷ እንሥራ አገርን አፍርሶ::
አገር ቆርሶ ጥሎ እንደ አሮጌ እቃ
ድንበሯ ይከበር እንውጣ ዘብ ጥበቃ
አቤት መቀላመድ አሁንም አይበቃ::
እድሜ ማራዘሚያ ለስልጣን መድሃኒት
ደግማችሁ ልትውጡት ለቀጣዩም ግንቦት
ሲባል እንዳል ነበር ቦዘኔ አደገኛ
የቅንጅት ደጋፊ የጎዳና ነውጠኛ
ወጣቱ ይደራጅ ይረከበን ከእኛ
ሰብስቦ ለማሰር አሁንም ዳግመኛ::
ትልቁ ማስታወሻ የወያኔ ሀውልት
የአቶ መለስ የሃያ ዓመት ቀዥት::

## *ከዚህ የበለጠ፡*

አዲሱ በአሮጌው ሊለጠፍ በተራ

የሥልጣን ኮርቻ ድልዳሉ ሲሠራ

ገና ከጧቱ ተዋሽተን ነበረ ሊሞላ ጎተራ

በቀን ሶስቴ በልተን ሊተረፈን እንጀራ

የባሰ ተርበን እየጠፋ አዝመራ

እንስሳው በዱር አልቆ እየበላው አሞራ

ለሰሚው ግራ ነው እንደው ባዶ ጉራ።

ህዝቤ አልተራበም አያወቀው መከራ

የምጣኔ እድገት ተብሎ ሲወራ።

በልቶ ማደር ሳይችል ከዳር እስከዳር

በሸንጎ መደንፋት በሃሰት ቀመር።

ዓለም ሲጮህልን ተጨንቆ ስለኛ

ስለእድገት ሲተርክ በውሸት መቶኛ

ከዚህ የበለጠ ከየት የምጣ ደበኛ።

ትልቁ ማስታወሻ የወያኔ ሀውለት

የመልስ ቀመር ነው የዜሮ ብዜት።

## ከውሸቶች ሁሉ፡

ሰንበት ካለው አውነት ካስመሰለው

ለእድሜ ማራዘሚያ በወቅቱ ካወራው

እንዳትሰለቹ ደግሜ ባወራው

በአገር በድንበር ሥም ወጣቱን የበለው

ከውሸቶች ሁሉ ዓለምን ያሳቀው

የወንድማማቾች ጥል የባደሜው ጉድ ነው

ሁለት ዓመት ሙሉ ተደርጎ ጦርነት

በድል ተጠናቆ ተሰጥቶ ሽልማት
ጉሮ ወሸባዬ እንዳልተባለለት
በራሱ አንደበት የጦሩ የበላይ
ድምፁን ከፍ አድርጎ «የባድሜን ጉዳይ
በጦር ሜዳ ሳይሆን የድንበሩን ድንጋይ
በዓለም አቀፍ ሽንጎ በሄግ ፍርድቤት
በቂ ማስረጃ አለኝ ያገኛል እልባት»
ብሎ ሲናገር ጀግኖች ሳለቁበት
ከዚህ የበለጠ ከየት ይምጣ ጠላት፡፡
ማለቂያ የሌለው የሰውዬ ቅጥፈት
አሁንም ሳይሰነብት ስለፍርዱ ሂደት
«የዓለም አቀፍ ሽንጎ ዳኛው ገለልተኛ
ውጤቱ ያማረ ተፈረደ ለእኛ
ደግማችሁ ሰልፍ ውጡ እሁንም ፍንደቃ
በዓይናችን እያየን ሲሆን ታጥቦ ጭቃ
ዓለም አቀፉ ጦር ቆሞ ዘብ ጥበቃ፡፡
ትልቁ ማስታወሻ የወያኔ ሀውልት
የባድሜን መሬት በካሣ መስጠት፡፡

*መሰሪ ጸባዩን፤*

እውነት አስመስሎ ቀጠለ ሊያወጋ
«ሆኜ አንድ ቁጥር በሰላም ፍለጋ
ሌሎች ሊከተሉኝ ከቆላ ከደጋ
እንቅፋት ባይሆነኝ የግንቦቱ ምርጫ
ቅንጅትን ፈጥሮ ባይበዛ ፍጥጫ
ተቸሮኝ አድናቆት፤ለኖቤል ሽልማት

ዓለምን ላነጫጫ፤ደግሜ በውሸት

አሸናፊነቴን ቀድሜ በማውሳት

ነበረ፤ማሰሬ ምሁርን በአንድነት፡፡

ደጋግመው ባይግቱኝ አፍዛ መድሓኒት

የማይገል የማይሽር የሚያቆም በውርደት

ብሎት እርፍ፤ አስመስሎ እውነት

ተፈጥሮ ሆኖበት ውሸቱን ሲያውቅበት

አዎ፤ይመስላል፤አለው ትንሽ እውነት፡፡

ቢሆንም፤ጣቱን ቀስሮ ቅንጅት ባይሚገት

መሰሪ ጸባዩን፤ማንም እይደርስበት፡፡

ሓይሉና ልደቱ ደርሰው ባያፈርሱት

ታሪክ ሠርቶ አልነበር የምሁሩ ዓብዮት፡፡

ትልቁ ማስታወሻ የወያኔ ሃውልት

ተለጣፊ ፈጥሮ በባንዳ መጫወት

## የለህም በህይወት፡፡

አቤት መዋሸት አሁንም መዋሸት

ውድድር እይደል አይስገኝ ሽልማት

ከላይ ሲወረወር ያከትመል በቅፅበት

ባንዳውም ሳይቀር ይጠፋል በድንገት፡፡

እባክህ አቶ መለስ ይብቃ መቀሳፈት

የሃያ ዓመት ውሸት አልሆነም አንድ እውነት፡፡

ቀድሞ ነበር እንጂ መሪ ሆኖ መገኘት

ጉድጎንድ ከተማሰ ከንቱነው መወትወት

የሚያዝያ ሰላሳው የለቅሶኛው ብዛት

ቋሚ ምሥክር ነው የለህም በህይወት፡፡
ትልቁ መስታወሻ የወያኔ ሃውልት
በቁሙ እየሞተ ሁልጊዜ መደንፋት፡፡

## የዋህ ካድሬዎቹ

እስቲ የሰሞኑን ትንሽ እንጫውት
የዋህ ካድሬዎቹ እምባ የረጩበት
መጠጊያ ፍለጋ የተራወጡበት
ጥሏቸው እንዳይጠፋ የተማፀኑበት
እውነቱን መስሏቸው እቃ እቃ ሲጫወት፡፡
«የአቅሜን ሠርቼ ሥልጣን ጠግቤለሁ
ሕውኃት ከለቀቀኝ ጡረታ ብያለሁ
ጥርቅም ውሸቴን መፅሃፍ እጽፋለሁ
ተረካቢ ይዘጋጅ ሁሉን ጨርሻለሁ»
«ከእኔ የተሻለ ውሻታም ማነው
ፈትሹ ፓርቲውን እኔ መሸሼ ነው»
አውሮፓ አሜሪካ የኸው ነበር ቃሉ
ዓለምን የዋሸው ዓመቱን በሙሉ፡፡
ወዲያው ቃሉን ሽሮ በፓርቲው አሳቦ
ምርጫ መሳተፉን በባንዳ ታጅቦ
ኃይሉና ልደቱን ከጎኑ አንግቦ
አፍጥጦ ብቅ ኣለ ዓይኑን በጨው ታጥቦ፡፡
ያለፈው ጠባሳ ቁስላችን ሳይሽር
አሁንም ምረጡኝ ከንቱ ግር ግር፡፡
አሁንም አይታፈር የምርጫ ዝገጅት

ከምንም ላያስጥል የባነዳ ክምችት፡፡
ከሆነ በምረጫ ካልሆነ በጡጫ
እድሜ ለማስረዘም ሌሊት ተቀን ሩጫ
ትልቁ መስታወሻ የወያኔ ሃውልት
ወዳጅ ጣለት ሣይል ሁሉንም መዋሸት፡፡

## *አይለቅም ሳይቀጣ፤*

የምርጫ ዘመቻ እቃ እቃ ጫወታ
የማያፍር ጉድ እምዬ አስጠግታ
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ
በውሸት ተሞልቶ እኔ ብቻ ጌታ
መድኃኔት የሌለው የሥልጣን በሽታ፡፡
እድሜ ለመቀጠል የአዋጁ ጋጋታ
መልካም እንደሠራ ሊከፈል ውለታ
ህዝብ ተሰብስቦ ሊሸኝ በእልልታ
በታሪክ አልታየም በሰላም ሲወጣ
እንኳን አንተን ቀርቶ ተልቁን ባለንጣ
አለመደም ቤቱ አይለቅም ሳይቀጣ፡፡
ትልቁ ማስታወሻ የወያኔ ሃውልት
የመለስ በሽታ የሥልጣን ጥማት፡፡

## *ዓይኑን ሳፈር ያለው፤*

ባካበትከው ውሸት በቁም ከመበላት
እውነቱን ተናግሮ የማይቀረውን ሙት፡፡
እንዴት አይባንንም አይገባውም እሱ
በቁሙ ሲቀብረው ሓይሌን ከነነፍሱ

ደርግን አሳብዶ ልመና ሲሰደው
ከልጅ እስከ አዋቂ ዓይኑን ለአፈር ያለው
እሱን የተሸላ ምንስ ሊቆየው ነው
የባእድ ቅጥረኛ መሆኑን ዘነጋው?
እውነትን ካመነ ስለማይቆይ በሕይወት
ሰውዬው ተለከፏል አይተውም መዋሸት።
ትልቁ ማስታወሻ የወያኔ ሃውልት
ህዝብን አማሮ ለመግዛት መመኘት።

***የክተቱን ጥሪ፤***

የወጋ ቢረሳ ተወጊ አይረሳ
ወቅቱ ቢቀያየር ቢበዛ አበሳ
ትውልድ ያድነዋል የአገሬን ጠባሳ።
ሕዝብን ገለል አርገው ፍቅር ካበዙበት
አድበቶ ሲቀጣ አለው ልዩ ብልሃት
አድባር አይለመን አያስጥል ጎረቤት
የኸው ነው ልማዱ የንጉሦቹም ቤት።
ትንሽ አይባንንም አይገባውም እንዴ
ሕዝብ አሰፍስፎ አንግቦ ጎራዴ
መመሪያ ሲጠብቅ ከአዝመች ፊታውራሪ
ብሶት ከሚፈጥረው ከአገር ተቆርቋሪ
የመጨረሻውን የክተቱን ጥሪ።
ትልቁ ማስታወሻ የወያኔ ሃውልት
የልቡ መደፈን በእብሪት መሞላት።

***የሰው ነህ ማደጎ፤***

ተፈጥሮን ተመክሮ ሆነና የማይገራው
የውሸት በሽታ ይዞት ሊጠፋ ነው።

ተብሎ የለ ማድረስ እንጂ ፈረስ

ጦር አይወረውር የአንጀት አያደርስ

ውርድ ከራስ ከእንግዲህ፤አቶ መለስ

ጆሮ ካለህ ስማ አታፍጥ በሽንጎ

ይሁን ተብሎ እንጂ <u>የሰው ነህ ማደጎ፡፡</u>

ትልቁ መስታወሻ የወያኔ ሃውልት

መንነቱን ረስቶ ህዝባዊነኝ ማለት፡፡

***ብርቱካን ሚደቅሳን፤***

የዛሬ ዝምታ የህዝባችን ትእግስት

ለቀጣዩ ቅጣት መሆኑን መሠረት

ጠንቋይ አይሻውም ቀድሞ ለመገመት፡፡

ምንድነው ከፍያው ለመለስ ምጸት

የአምላክ ቁጣ ብሎ ለጥብሎ መገዛት

እንደ ባንዳዎቹ ትራፊ ለማግኘት

ወይስ መዘጋጀት ለመክፈል መስዋእት

ብርቱካን ሚደቅሳን ሺህ ሆነን መነሳት፡፡

አጉል መዳፈሩ የሺዎችን እናት

የታሰረች መስሎት መንፈሱ አግኗት

የዓለም መሪ ሆና ሁሉም አሞግሷት

ቅናት አቃጠለው ታስራም ቀደመችው

የተማረ መስሎት ገብቶ ሊቃጠል ነው፡፡

ትልቁ ማስታወሻ የወያኔ ሃውልት

በቅንጅት መንፈስ መጫወቱ በእሳት፡፡

**ባዩህ ዛሬ**

**ግንቦት/2002**